# ቅንጅት ዓለም አቅፍ ላዕላይ ምክር ቤት

**Kinijit International Council**

**www.KINIJIT.org**

ሰኔ 17 ቀን 1999 ዓ.ም.

# የቅንጅት ዓለም አቀፍ ላእላይ ምክር ቤት መስራች ስብሰባ በአጥጋቢ ሁኔታ ተካሄደ፡፡

__መግለጫ - 2__

ከ ቃሊቲ የቅንጅት አመራር በተሰጠዉ አቅጣጫ ትእዛዝና አደራ መሰረት በመጡት አስታራቂ ልዑካን ዶ/ር በዛብህ ደምሴና ሻለቃ አድማሱ መላኩ ጥረት የቅንጅት ዓለም አቀፍ ላእላይ ም/ቤት መስራች ስበሰባ ዛሬ ጁን 24 2007 በክራዉን ፐላዛ ሆቲል ሲልቨር ስፐሪንግ ሜሪላንድ ዩ.ኤስ.ኤ በአጥጋቢ ሁኔታ ስራዉን አከሂዷል፡፡ አዲስ አመራር ዲሞክራሲያዊ በሆነ መልክ በመተሳሰብ፤ በመከባበርና በመተማመን ኩሀሉም በላይ የቅንጅትን መርሆ በተመከተልና በአዲስና በጠነከረ መሰረት በአንድ ድምጽ ለመናገር ለአንድ ቅንጅት ለመስራት በአንድነት ለመቆም ለኢትዮጵያ ህዝብ ለዲያስፖራሲ ለታሰሩ ወገኖች ለሴቶች ለወጣቶች አርአያ ለመሆን ቃል የገባዉ ይህ ስብሰባ ከጁን 23 እሰከ ጁን 24 ባከሄደዉ ስብሰባ 22 ተሳታፊዎች ከአሜሪካ ከካናዳና አዉሮፓ ተገኝተዉ ተሳትፈዋል፡፡

አስታራቂ ቡድኑ ለ23 ግለሰቦች በጽሑፍና በሌላም መገናኛ ዘዴ በስብሰባዉ እንዲገኙ ያልተቆጠበ ጥረት አድርጓል፡፡ ስብሰባዉና ምርጫዉ ለሁሉም ተጠሪዎች ክፍት ከመሆኑም በላይ መንፈሱ ያልተገኙም የቅንጅት ዓለም አቀፍ መማክርት አሁንም ቢሆን አዲሱ ዓለም አቀፍ ም/ቤትና አመራር ገብተዉ እንዲሰሩና ለቅንጅት በአዲስ መንፈስ አስተዋጽኦ እንዲደርጉ ጥሪዉን አቅርቧል፡፡

በዚህ አዲስ መንፈስ ብሩህ አሰተሳሰብ የወደፊት ተግባር ላይ ያተኮረዉ ስብሰባ የሚከተሉትን ዉሳኔዎች አስተላልፏል፡፡

1ኛ/ ዘጠኝ አባላት ያሉትን የሥራ አስኪያጅ ኮሚቲ አባላት ዲሞክራሲዊ በሆነ መንገድ መርጧል፡፡

2ኛ/ አጀንዳ በማዉጣት ም/ቤቱ በሰዉ ኃይልና በመዋቅር ለማጠናከር ብዙሃንን ለማከተት ወጣቶችንና ሴቶችን የሐጉር ተወከዮችን የሙያ ድርጅቶችን የሚሰበስብ ሥራ በሁለት ሳምንት ዉስጥ የተቀነባበረ በጥናት የተመሰረተ ለቅንጅት ጠቃሚ የሆነ ደጋፊዎችን ሁሉ የሚያቅፍና የሚያበረታታ ሁለገብ ሃሳብ (proposal) ለቅንጅት ዓለም አቀፍ ላእላይ ምክር ቤት እንዲቀርቡ በድርጅትና በጥናት ምርምር ኮሚቲ ሓላፊዎች የሚመራ የስራ ቡድን አቋቁሟል፡፡ ይህ የስራ ቡድን ችሎታና ሙያ ያላቸዉን ግለሰቦችና መሪዎች እያነጋገረ ሥራዉን በሁለት ሳምንት ዉስጥ እንዲያቀርብ ተወስኗል፡፡

ከዚህ አያይዞ ይኸዉ ቡድን ለም/ቤቱ ስብሰባዉ ከቤቱ የተሰጠዉና ከዚህ በፊት የታመኑ መረጃዎችን በተባለዉ ጊዜ ገደብ ዉሰጥ የባህርይ መመሪያ (code of conduct) አርቅቆ እንዲያቀርብ ተጠይቋል፡፡

3ኛ/ ስብሰባዉ የቅንጅትን ድጋፍ ለማጠናከር በሰሜን አሜሪከ የሚገኙ ደጋፊ ቅርንጫፎችና ድርጅቶች በስምምነት በመደጋገፍ በመተባበር ለአንድ ዓላማ ለመስራት መቻል አንዳለባቸዉ

ግንዛቤ አድርጓል። በአሁኑ ወቅት ያሉ ልዩነቶችን በዉይይት መፍታት አስፈላጊ መሆኑንም አምኖበታል። ለዚህ ይረዱ ዘንድ በመጀመሪያ በስብሰባዉ ያልተገኙትን ከዚህ በፊት የቅንጅት ዓለም ዓቀፍ አመራር አባላት የነበሩትን 6 (ስድሰት) ደጋፊዎች በእየግል በማነጋገርና ለአዲሱ ም/ቤት ሙሉ ተሳታፊነትና አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ስድስት አባላት የያዘ የሥራ ቡድን መርጧል። እነዚህ ግለሰቦች ለቅንጅት የደከሙ፡ አስተዋጽኦ ያደረጉ ብቁነትና ችሎታ እንዳላቸዉ ተስማምቷል። ይህ ችግር ሲፈታ በቅርንጫፎችና ደጋፊ ድርጅቶች መካከልም ያለዉ አለመግባባት እንደሚፈታ አምኗል። የስራ ቡድኑ ይህን ተግባር በሁለት ሳምንት ዉስጥ አጠናቆ ለቤቱ እንዲያቀርብ ተጠይቋል።

4ኛ/ ስብሰባዉ የቅንጅት ዓለም አቀፍ ላእላይ ም/ቤት ካለፈዉ ልምድ በመማር የገንዘብ (Finance) አሰራር በዘመናዊ መንገድ እንዲሰራ ተስማምቷል። በዚህም መሰረት ከፋይናንስ ኃላፊዉ ጋር ሆነዉ የሚሰሩ ሁለት አባላት መርጦ የሂሳብ አያያዝ ሥራ እቅድ የሚያዘጋጅ ኮሚቲ መርጧል። ይህ ቡድን ሥራዉን በሁለት ሳምንት ዉስጥ ለም/ቤቱ እንዲያቀርቡ ተስማምቷል። በዚህም ዙርያ በአሁኑ ጊዜ የሚያጠያይቀዉ የቅንጅት የገንዘብ አያያዝ ሁኔታ ነጻ በሆነ ኦዲተር ተጠንቶና ተመርምሮ ዉጤቱ ለም/ቤቱና ለህዝብ እንዲቀርብ ተሰማምቷል።

5ኛ/ የህጋዊነት (Legal Status) ጥያቄን የሬዲዮንና ዌብሳይት አያያዝና አጠቃቀምን በተመለከተ ስበሰባዉ እነዚህ ለቅንጅት ጠቃሚ በሆነ መንገድ እንዲጣመሩና እንዲያዙ ማስፈለጉን ተሰማምቷል። ዉሳኔ ለማቅረብ እንዲመች ሰበሰባዉ አራት አባላት የያዘ የሥራ ኮሚቲ ሰይሞ ይህ ኮሚቲ ሥራዉን በሁለት ሳምንት አጠናቆ እንዲያቀርብ ጠርቷል።

6ኛ/ ም/ቤቱ ከአሁን ጀምሮ አመርቂ የሆነ ዉጤት ለማስገኘት እያንዳንዱ ዘርፍ የአጭርና የረዥም ጊዜ ሥራዉን በዕቅድ እንዲከታተል ተስማምቷል። በዚህም መሠረት የእያንዳንዱ ዘርፍ ኃላፊ የሥራዉን ትልም (Term of Reference) በሁለት ሳምንት ዉስጥ ለም/ቤቱ እንዲያቀርብ ተሰማምቷል።

7ኛ/ ስብሰባዉ በአጭር ጊዜ ዉስጥ የሚሰራቸዉን የተግባር ቅደም ተከተል ተወያይቶ የሚከተሉትን ዉሳኔዎች ላይ ተሰማምቷል።

ሀ/ ሊቀ መንበሩና ሁለቱ አስታራቂ ወንድሞቻችን በሶስት ወርና በስድስት ወር መደበኛ ስብሰባ እንዲያደርጉ ወሳኗል።

ለ/ ስብሰባዉ አመራሩ ከልዩ ልዩ ተቃዋሚ ድርጅቶች ጋር የተጀመሩ ግንኙነቶችና ወደፊተም መደረግ ያለባቸዉን ግንኝነቶች በፍጥነት ማድረግ እንዳለበት ተሰምምቷል።

ሐ) ከAFD ጋር ያለዉ ግንኘነት በጠነከረ ሁኔታ እንዲራመድ ከስራ አሰኪያጅ ኮሚቲዉ አደራዉን ገልጧል።

የቅንጅት ዓለም አቀፍ ላእላይ ምክር ቤት

**JUNE 23, 2007**



**8605 Cameron Street, Suite M- Silver Spring, MD 20910**
**Tel: (202)541-9507, Fax: (202)541-1090**
**Email: KIC@kinijit.org**